# የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ ለማስጠትና ለማቋረጥ የሚቀርቡ ውሳኔዎች የሚጣራበትን አግባብ ለመወሰን የወጣ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 809/2013

ሀምሌ 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የማዕድን ስራዎች የፈቃድ አሰጣጥ ተግባርን እንዲያከናወን የተቋቋመው ዳይሬክቶሬት አግባብ ባለው ሁኔታ ፈቃድ አሰጣጥ ስራውን ማከናወኑን ለማረጋገጥና ማስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች ፈቃዱ ከማስጠቱ በፊት ታይቶ ማስተካከል እንዲችል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በማዕድን ልማት ላይ ለመሳተፍ የሚጠይቁ ግለሰቦችና ድርጅቶች ለስራው በቂ እወቀት፣ ልምድና ገንዘብ ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥና ፍትሀዊ በሆነ ሜኩ ፈቃዶችን ማስጠት እንዲቻል፤

በፈቃደ አሰጣጡ ሂደት ላይ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች መሳተፍ እንዲችሉና ከፈቃድ ጠያቂው የሚቀርቡ ሰነዶችን በአግባቡና ከማዕድን አዋጁና ደንቡ አኳያ መገምገሙ ማረጋገጥ እንዲቻል ለማድረግ፤

የማዕድን ሀብት ልማት ስራ በአካባቢና በህብረተሰቡ ላይ ጉዳት ሳያስከትል መመረት እንዲችል ማድረግና የሀብቱ ባለቤት የሆነው መንግስትና ህዝብም ከምርቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ እንዲቻል፤

እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስ የተለየ መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፤

ይህ መመሪያ በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁ. 678/2002 አንቀጽ 82 (2) በተሰጠው ስልጣን ማስረት ተዘጋጅቷል፡፡

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የማዕድን ስራዎች ፈቃድ ለማስጠትና ለማቋረጥ የሚቀርቡ ወሳኔዎች የሚገራበትን አግባብ ለመወሰን የወጣ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 809/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ወስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆን በስተቀር፡

1. ለማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁ. 678/2002 (በአዋጅ ቁ. 816/2006 እና 1213/2012 እንደተሻሻለው)፤ እንዲሁም የማዕድን ስራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 423/2010 የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2. "የማዕድን ሕግ" ማለት እንደ አግባቡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱትን ሕጎችን ያካትታል፡፡
3. "የማዕድን ስራዎች ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት አጣሪ ኮሚቴ" / ከዚህ በኋላ ኮሚቴ እየተባለ የሚገለፀው/ ማለት የማዕድን ስራ ፈቃድ ማስጠት እንዲቻል በማዕድን ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ተዘጋጅቶ ለበላይ አመራር ቀርቦ የተመራለትን የፈቃድ ማስጠት ሰነድ አጣርቶ ለበላይ አመራር የወሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተቋቋመ አካል ነው፡፡

## 3. አላማ

ይህ መመሪያ የሚከተሉት አላማዎች ኖሩታል፤

1. የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱ በተወሰኑ ሰዎች ተሳትፎ ብቻ የሚከናወን እንዳይሆንና የተለያዩ የሙያ ስብጥር ያላቸው ባለሙያዎች በሂደቱ ላይ ተሳትፈው ጥራት ያለው ስራ ማከራት እንዲቻል፤
2. የማዕድን ስራ ፈቃድ ከማስጠቱ በፊት በማዕድን ሕጎች ማስረት መንግስትና ሕዝብ ሊያገኙ የሚገባቸው ጥቅሞች በአግባቡ መካተታቸውን ለማረጋገጥ፤
3. የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ የጋራ ሀላፊነት እንዲሁም አሳታፊነትን ማስረት አድርጎ የሚከናወን እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሚኒስቴር ማስሪያ ቤቱ በሚሰጡ የማዕድን ስራዎች ፈቃድ ላይ ብቻ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## 5. የፈቃድ አሰጣጥ ሂደት

1. የአካባቢና ማሕበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ መከናወኑንና በሚመለከተው አካል ይሁንታ አግኝቶ መቅረቡን ማረጋገጫ ይቀርባል፤
2. በፈቃድ ጠያቂ የቀረበው የሥራ እቅድ በማዕድን ሕጎቹና በሚኒስቴሩ በተዘጋጁት ማስፈርቶች ማስረት መቅረቡን በማዕድን ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ባለሙያ ተገምግሞ እና ተጣርቶ ወጤቱ ለፈቃድ ቡድን አስተባባሪ ይቀርባል፤
3. የፈቃድ ቡድን አስተባባሪ የቀረበለትን የፈቃድ ሰነድ የራሱን የማጣራት ስራ ከካናወነ በኋላ ለማዕድን ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ያቀርባል፡፡
4. የማዕድን ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርም ከፈቃድ ቡድን አስተባባሪ የቀረበለትን ሰነድ በራሱ ደረጃ አጣርቶ፤ በግምገማ ወቅት የተሟሉትንና የጎደሉ ነገሮችን በማየት ለንጽጽር በሚያመች ቅጽ አዘጋጅቶ ከፈቃድ ጠያቂ ሰነድ ጋር በማያያዝ የወሳኔ ሀሳብ ለበላይ አመራር ያቀርባል፤
5. የበላይ አመራሩ ከስራ ክፍሉ የቀረበለትን ማስታወሻና ሰነዶች እንዲጣሩና የወሳኔ ሀሳብ እንዲቀርብለት ለኮሚቴው ይመራል፤

## 6. የፈቃድ ኮሚቴ አባላት

በማዕድን ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ተገምግሞ የቀረበወን የፈቃድ ጥያቄና ሰነዶችን በመገምገም ለበላይ አመራሩ የወሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ የኮሚቴ አባላት በበላይ አመራሩ የሚሠየሙ ሆነው የሚከተለወን የሙያ ስብጥር ያካተተ ሰባት (7) አባላት ይኖሩታል፤ሆኖም ለወሳኔ ድምጽ ማስጠት የመቻሉት ከተራ ቁጥር 1- 4 ያሉት አምስቱ አባላት ብቻ ይሆናሉ፤

1. አንድ ሰው ስለ ፈቃድ አሰጣጥ ግንዛቤ ያለው ሰብሳቢ፤

2. ልምዱ ካላቸው የስነ ምድር ባለሙያዎች 2 ሰው አባል፤

3. የሚኒራል ኢኮኖሚ ባለሙያ 1 ሰው አባል፤

5. ከሕግ ጉዳዮች ዳሬክቶሬት 1 ሰው አባል፤

6. የማዕድን ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አስረጅ፤

7. አንድ ሰው ድምጽ አልባ ፀሐፊ ፡፡

## 7.የኮሚቴው ተግባርና ሀላፊነት

ኮሚቴው በማዕድን ፈቃድ ዳሬክቶሬት ተገምግመው ለበላይ ሀላፊ የቀረቡና የተመራለትን የፈቃድ ጥያቄ ሰነድ ከማዕድን ሕጎችና ስራው ከሚጠይቀው ቴክኒክ አግባቡ መገምገማቸውን ከዚህ መመሪያ ሜጨረሻ ላይ በተያያዘው ቼክ ሊስት ማስረት በማጣራት ለበላይ አመራሩ የወሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

### 7.1 ለምርመራ ፈቃድ ጥያቄ የሚቀርብ ማመልከቻ ሲሆን

ሀ. የኩባንያው መግለጫ (ፕሮፋይል) ተጣርቶ መቅረቡን፤

ለ. የስራ ዕቅድ መቅረቡን፤

ሐ. ፈቃድ የተጠየቀበት ቦታ በሌላ ባለፈቃድ አለመያዙን የሚያረጋግጥ በካዳስተር የተመዘገበ መሆኑን የሚያሳይ መግለጫ፤

መ. ለስራው የተመደበው በጀት ቢያንስ የመጀመሪያውን አመት ሥራ ለማሰራት በቂ መሆኑን፤

ሠ. በጋዜጣ መውጣቱንና ተቃውሞ ያልቀረበበት መሆኑን፤ ተቃውሞም ቀርቦበት ከሆነም መፍቴህ ማግኘቱን፤

ረ. የፈቃድ ማመልከቻ የቀረበበት ቦታ በክልል ፈቃድ ያልተሰጠበት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፤

ሰ. ፈቃድ የተጠየቀበት የማዕድን ስራ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ መደረጉንና ከሚመለከተው የመንግስት አካል ይሁንታ አግኝቶ መቅረቡን፤

ሸ. እንደማዕድኑ አይነት ፈቃድ የተጠየቀበት ቦታ የቦታ ስፋት በሕጉ ማስረት መሆኑን፤

ቀ. ፈቃድ ጠያቂው በተቀመጠው ማስፈርት ማስረት 70 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ውጤት ያገኘ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፤

ተ. የቀረበው የፈቃድ ጥያቄ ለደለል ወርቅ ከሆነ፤ የምርመራ ስራ ፕሮግራሙ የፊዚቢሊቲ ጥናቱን ጨምሮ ከአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ መሆኑን የሚያሳይ መግለጫ መቅረቡን፤

**7.2 የምርመራ ፈቃድን ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ሲሆን፤**

ሀ. የፈቃድ እድሳት ጥያቄው የመጀመሪያው የፈቃድ ዘመን ከማለቁ ከስልሳ (60) ቀናት በፊት የቀረበ መሆኑን፤

ለ. በማዕድን ስራዎች ሕጎች ድንጋጌዎች እና በውሉ ማሰረት ባለፈቃዱ ባለፈው የፈቃድ ዘመን ግዴታዎቹን የተወጣ ስለመሆኑ በስራ ክፍሉ ተገምግመው ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፣

ሐ. ማሟላት የሚገባቸው ዝርዝር መረጃዎች ተሟልተው መቅረባቸውን እና መቅረብ የሚገባቸው ሪፖርቶች ቀርበው በስራ ክፍሉ ተገምግመው ተቀባይነት ማግኘታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ፤

መ. በማዕድን ስራዎች ሕግ ማሰረት ከፈቃድ ቦታው ላይ ሚለቀቅ የሚገባውን መሬት በመቀነስ ዕድሳት የጠየቀበትን ቦታ የሚያመለክት የጂኦግራፊክ ኮኦርድኔት የያዘ መግለጫ መቅረቡን፤

ሠ. ባለፈው የፈቃድ ዘመን ስራዎች ወቅት የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ የአካባቢና የማሕበረሰብ ተፅዕኖ ኦዲት እና ለቀጣይ ፈቃድ ዘመን የተዘጋጀው የአካባቢና የማሕበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ከሚመለከተው አካል ይሁንታ ማግኘታቸውን መግለጫ፤

**7.3. ለምርት ፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ ሲሆን፤**

ሀ. ፈቃድ የተጠየቀበት ማመልከቻ ከነ አዋጭነት ጥናት ሰነድ መቅረቡን፤

ለ. የኩባንያው መግለጫ (ፕሮፋይል) መቅረቡን፤

ሐ. ከስራ ክፍሉ የቀረበ የአዋጭነት ጥናት ጥቅል መግለጫ፤

መ. ለተጠየቀው ማዕድን ማምረት ፈቃድ ቦታ የተሟላ የአካባቢና ማሕበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ መካሄዱንና ይሁንታ ማግኘቱን የሚያሳይ መግለጫ፤

ሠ. እንደማዕድኑ አይነት ፈቃድ የተጠየቀበት ቦታ ስፋት በሕጉ ማሰረት መሆኑን የሚያሳይ መግለጫ፤

ረ. ባለፈቃዱ በማዕድን ሕጉና በስምምነቱ ማሰረት በምርመራ ፈቃድ ወቅት ሊወጣ የሚገባቸውን ግዴታዎች የተወጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤

7.4 **የምርት ፈቃድን ለማደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ሲሆን፤**

ሀ. ማመልከቻው የመጀመሪያው የፈቃድ ዘመን ከሚፈፀሙ ከ180 (ከመቶ ሰማንያ) ቀናት በፊት የቀረበ መሆኑ፤

ለ. በማዕድን ሕጎች ድንጋጌዎች እና በወሉ መሰረት ባለፈው የፈቃድ ዘመን ግዴታዎቹን የተወጣ ስለመሆኑ በስራ ክፍሉ ተገምግመው ተቀባይነት ማግኘታቸውን የሚገልጽ መግለጫ፤

ሐ. ባለፈው የፈቃድ ዘመን መቅረብ የሚገባቸውን ሪፖርቶች ቀርበው በስራ ክፍሉ ተገምግመው ተቀባይነት ማግኘታቸወን የሚገልጽ መግለጫ፤

መ. የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽኖ አዲትና ፈቃዱ ለሚታደስበት ዘመን የአካባቢና የማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ለሚከከተው አካል ቀርቦ ይሁንታ ማግኘቱን የሚያሳይ መግለጫ፤

## 7.5 ይዞ ለመቆየት ፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ ሲሆን፤

ሀ. ክምችቱን ወደ ምርት ለማሸጋገር ያልተቻለበትን ሁኔታ የሚያስረዱ መረጃዎች ተያይዘው መቅረባቸውን፣

ለ. ክምችቱን ወደ ምርት ለማሸጋገር ያልተቻለበትን ሁኔታ የሚያስረዱ መረጃዎች ተገምግመው መግለጫ መቅረባቸውን፤

## 7.6 ፈቃድን ለማስተላለፍ የሚቀርብ ማመልከቻ ሲሆን

ሀ. የዝወወር ፈቃዱ እንዲተላለፍ ለማስፈቀድ የቀረበ ማመልከቻ ኮፒ፤

ለ. ፈቃዱን ለማስተላለፍ የተደረገ ስምምነት በሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ ጽ/ቤት ተረጋግጦ መቅረቡን የሚያሳይ ማስረጃ፤

ሐ. ፈቃድ የሚተላለፍለት ሰው በማዕድን ሕጉ መሰረት በቂ የገንዘብ አቅምና የቴክኒክ ብቃት ያለው ስለመሆኑ መግለጫ፤

መ. ፈቃድ የሚተላለፍለት ሰው በማዕድን ሕጉ መሰረት የተፈቀደለት ሰው ስለመሆኑ መግለጫ መቅረቡን፤

ሠ. በገቢ ግብር ሕግ መሰረት በፈቃድ ወይም በአክሲዮን ማስተላለፍ ዋጋ ላይ ትርፍ ተገኝቶ ከሆነ ከትርፍ ድርሻው ግብር ስለመከፈሉ ከግብር ሰበሳቢ መስሪያ ቤት ማረጋገጫ መቅረቡን፤

ረ. ባለፈቃዱ በማዕድን ሕጉና በስምምነቱ መሰረት ግዴታዎቹን የተወጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤

ሰ. ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው በማዕድን ስራዎች ሕግ፣ በፈቃድ ስምምነቶችና በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሰረት በፈቃድ አስተላላፊው የተገቡትን ግዴታዎች አክብሮ ለመፈፀም ግዴታ መግባቱን የሚያረጋግጥ መግለጫ፤

ሸ. ፈቃድ እንዲተላለፍለት የተጠየቀለት ሰው የምርመራ ፈቃድ ከሆነ የቀረበው የስራ ፕሮግራም፤ የምርት ፈቃድ ከሆነ ደግሞ የቀረበው የምርት ፕሮግራም ተቀባይነት ማግኘታቸውን የሚገልጽ መግለጫ፤

## 8. ፈቃድ ለማስረዝ የሚቀርብ ሀሳብ

የማዕድን ስራዎች ፈቃድን ለማቋረጥ (ለማስረዝ) ከፈቃድ ዳይሬክቶሬት ለበላይ አመራሩ የሚቀረብ ማስታወሻ እንደሁኔታው የሚከተሉትን ማካያዎች የያዘ መሆን አለበት፡፡

1. ፈቃዱ የተሰጠበት ጊዜና አሁን ያለበትን ደረጃ (የፀና ፈቃድ ስለመኖሩ)፣ ስለአፈጻጸም ጉድለቱ በስራ ክፍሉ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ስለመኖሩ የሚያሳይ መግለጫ፤
2. ባለፈቃዱ ደካማ አፈጻጸም ባሳየበት የስራ ዘመን የነበረውን ዝቀተኛ አፈጻጸም የሚያሳይ አጭር መግለጫ፤
3. ባለፈቃዱ በማዕድን ሕጉ መሰረት ለመንግስትም ሆነ ለማህበረሰብ የሚኖርበትን ግዴታዎች የተወጣበትን አፈጻጸም የሚያሳይ መግለጫ፤
4. ባለፈቃዱ ከአካባቢ ጥበቃና ከማህበረሰብ ጤንነትና ደህንነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ ያለው አፈጻፀም መግለጫ፤

## 9. የስብሳባ ሥነስርአት

ሀ. የኮሚቴው የስብሰባ ቀንና ሰአት በኮሚቴው አባላት ይወሰናል፤

ለ. የፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ ግምገማ ውጤት ለኮሚቴው ከበላይ አመራር እንደተላከ የኮሚቴው ሰብሳቢ በሰባት የስራ ቀናት ወስጥ ስብሰባ ይጠራል፡፡

ሐ. የኮሚቴው አብላጫ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

መ. ማናቸውም የውሳኔ ሀሳቦች በድምጽ ብልጫ የሚያልፍ ሲሆን ባስረጂነትና በፀሐፊነት የሚሞዱቡት አባላት ድምጽ አይኖራቸውም፤ ድምጽ እኩል በሆነ ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤

## 10. የውሳኔ ሀሳብ

ሀ. ኮሚቴው በበላይ አመራር የቀረበለትን የማዕድን ስራዎች ፍቃድ ግምገማ ውጤቶችን በማጣራት፤ የምርመራ ፈቃድ ሲሆን በ5 የስራ ቀናት ወስጥ፤ የምርት ፈቃድ ሲሆን ደገሞ እንደ ማዕድኑ ዓይነትና ሁኔታ ጊዜው የሚወሰን ሆኖ በተቻለ ፍጥነት የውሳኔ ሀሳቡን ለበላይ አመራር ማቅረብ አለበት፤

ለ. በተራ ቁጥር አንድ የተገለፀው ለበላይ አመራር የሚቀርበው የውሳኔ ሀሳብ በኮሚቴው አባላት የተፈረመ ቃለ ጉባኤ መሆን አለበት፤

## 11. የተሻረ መመሪያ

የማዕድን ስራዎች ፈቃድ ማሜልከቻዎች ለማስተናገድ የተዘጋጀ የወስጥ አሰራር መመሪያ ቁጥር 4/2011 ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

## 12. መመሪያው ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ የማዕድን ስራዎች ፈቃድ አሰጣጥ ሂደትን ለመወሰን የወጣ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበት ከነሀሴ 12 ቀን 2013 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ኢንጂነር ታከለ ኡማ

የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ሚኒስትር

አዲስ አበባ

ነሀሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም